EARLY CHILDHOOD EDUCATOR
PAY EQUITY FUND

# የመረጃ ክፍለ-ጊዜ

ኖቬምበር 1፣ 2022

AIDKIT

OSSE

WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዲሲ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች እንኳን በደህና መጣችሁ!



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የዙም ተሳትፎ

ጥያቄዎችዎን የ Q&A feature (**የጥያቄና መልስ ምልክትን**) በመጠቀም ያስገቡ።

ቀድመው መውጣት ይፈልጋሉ? በማንኛውም ጊዜ **ከስብሰባ ይውጡ** አዝራርን ይጫኑ።





ወደ **መገልገያ ጽሁፎች** የሚወስዱ ተጨማሪ **መረጃዎች** እና **ማስፈንጠሪያዎች** እዚህ ይጋራሉ።

ምርጫዎ በሆነ ቋንቋ ስብሰባውን ያዳምጡ። **የአማርኛ** ወይም **የስፓንኛ አስተርጓሚን** ለማግኘት እዚህ ይጫኑ።

# በቀጥታ የሚተላለፉ ጥያቄዎች እና መልሶች









ጥያቄዎን እዚህ ይጻፉ እና ያስገቡ የምለውን ይጫኑ።

# የዛሬ ተናጋሪዎች ጋር ተዋወቁ

- ሳራ ሚድ፣ ለቅድመ ትምህርት ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ፣ OSSE
- ሩቲ ተስፋዬ፣ ቀዳሚ የፕሮግራም አስተዳዳሪ፣ AidKit





# የስብሰባ ዓላማዎች

- የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍን እና በ2023 (FY23) በጀት ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ እንዴት እንደሚሰራ ማስተዋወቅ
- ለFY23፣ የብቃት መስፈርቶች፣ የማመልከቻ የጊዜ ቅደምተከተል፣ ማን ማመልከት እንዳለበት፣ የስርጭት መርሃ ግብር እና የቀረበውን የቴክኒክ ድጋፍ ጨምሮ የማመልከቻውን ሂደት ማብራራት

# አጀንዳ


1. የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የፍትሃዊ ክፍፍል እርዳታ መግቢያ
2. ነትስ እና ቦልትስ፥ ለተጨማሪ ክፍያ ማመልከት
3. የመዝጊያ እና ቀጣይ እርምጃዎች

AIDKIT OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ለኤርሊ ቻይልድሁድ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ማመልከቻ ለማስገባት አቅደዋል?

እባክዎ በማያ ላይ ለዙም ምርጫ ምላሽ ይስጡ



# የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ የፍትሃዊ ክፍፍል እርዳታ መግቢያ



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# እንዴት ነው እዚህ የደረስነው

- [የቅደመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ ክፍፍል ካሳ አጣሪ ቡድን ጊዜያዊ ማሻሻያ ሕግ](#) [በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ፍትሃዊ ክፍፍል ካሳ አጣሪ ቡድን](#) ምክረ-ሀሳቦች መሰረት ለቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች የክፍያ እኩልነትን ለመደገፍ የክፍያ ፍትሃዊ ክፍፍል እርዳታዎችን እንዲሰራጭ ለOSSE ስልጣን ሰጥቶታል።
- የስራ ሃይሉ OSSE ለሚያደራድር ድርጅት ጋር አጋር በመሆን በ FY22 እና FY23 ለተጨማሪ ክፍያዎች ብቁ ለሆኑ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች እንዲያከፋፍል ከዚያም የገንዘብ ድጋፍን ጨምሮ በFY24 ወደ ኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች መደበኛ የክፍያ ቼክ አካል እንዲሸጋገር አዟል።
- OSSE የቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ ክፍፍል እርዳታን እንዲያድል AidKitን መርጧል።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ተጨማሪ ክፍያዎች የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያን ለመጨመር የረጅም-ጊዜ ጥረት መጀመሪያ ናቸው




| FY22 (ኦክቶበር 1, 2021-ሴፕቴምበር 30, 2022) | FY23 (ኦክቶበር 1, 2022-ሴፕቴምበር 30, 2023) | FY24 (ኦክቶበር 1, 2023-ሴፕቴምበር 30, 2024) |
|---|---|---|

# የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ በ FY23 እንዴት ይሰራል

OSSE እና AidKit በ FY23 ገንዘቦችን በቀጥታ ለቀድሞ አስተማሪዎች ማሰራጨታቸውን ይቀጥላሉ፣ ነገር ግን በአራት የሩብ አመት ክፍያዎች ነው።

| የሩብ አመት ክፍያ ስርጭት ወር | በሚከተለው ላይ ወይም ከዚያ በፊት የተቀጠረ መሆን አለበት | ECE I መጠን | ECE II መጠን |
|---|---|---|---|
| ዲሴምበር 2022 | ኖቬምበር 1፣ 2022 | $2,500 | $3,500 |
| ማርች 2023 | ፌብሩዋሪ 1፣ 2023 | $2,500 | $3,500 |
| ጁን 2023 | ሜይ 1፣ 2023 | $2,500 | $3,500 |
| ሴፕቴምበር 2023 | ኦገስት 1፣ 2023 | $2,500 | $3,500 |

- ክፍያ ለመቀበል፣ አንድ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ከላይ በተዘረዘሩት ቀናት፣ ወይም ከዚያ በፊት፣ እና ክፍያ በተከፈለበት ቀን መቅጠር አለበት።
- ECE I የሚያካትተው:- ረዳት መምህር፣ ተባባሪ ተንከባካቢ፣ የሞንቴሶሪ ረዳት መምህር
- ECE II የሚያካትተው:- አስተማሪ፣ ቤት/የተስፋፋ የቤት አቅራቢ፣ የሞንቴሶሪ መምህር
- የትርፍ ሰዓት ሰራተኞች ከጠቅላላው የክፍያ መጠን ግማሹን ይቀበላሉ

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የብቁነት ፖሊሲ

በ FY23 ከኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊ የገንዘብ ድጋፍ ተጨማሪ ክፍያዎችን ለመቀበል ብቁ ለመሆን፣ አንድ ግለሰብ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፦

1. በአሁኑ ጊዜ በOSSE ፈቃድ ባለው የህጻን እድገት ተቋም ውስጥ የተቀጠረ እና በአንድ ሳምንት ቢያንስ 10 ሰአታት የሚሰራ
2. **ብቁ በሆነ ሚና** ውስጥ **ተቀጣሪ** መሆን።
3. **የተጨማሪ የክፍያ ጥያቄን** ለ AidKit ማስገባት።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# 1. በOSSE ፈቃድ ባለው የህጻን እድገት ተቋም ውስጥ የተቀጠረ እና በአንድ ሳምንት ቢያንስ 10 ሰአታት የሚሰራ

በOSSE ፍቃድ የተሰጠው የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ ተቆጥሮ እየሰራ እንደሆነ ተደርጎ ለመወሰድ፣ አመልካች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለብዎት፥

በOSSE ፍቃድ የተሰጠው የልጅ እድገት ተቋም ውስጥ ተቀጥሮ መስራት፥

- ክፍያ ከተሰራጨበት ወር በፊት ወይም ከወሩ የመጀመሪያ ቀን በፊት (ለምሳሌ፣ ኖቬምበር 1፣ 2022፡- ፌብሩዋሪ 1፣ 2023፤ ሜይ 1፣ 2023 እና ኦገስት 1፣2023)
- ማመልከቻቸውን በሚያስገቡበት ጊዜ፤ እና
- የገንዘብ እርዳታዎች በሚከፋፈሉበት ጊዜ።

ማሳሰቢያ፥ በOSSE ፈቃድ በሌላቸው ተቋማት ያሉ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች ለእነዚህ የገንዘብ ድጋፎች ብቁ አይደሉም፣ ይህ በ DC የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ወይም በገለልተኛ የህዝብ ትምህርት ቤት የተቀጠሩ ሰራተኞችን ይጨምራል።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# 2. ብቁ በሆነ ሚና ውስጥ ተቀጣሪ የመሆን

ብቁ በሆነ ሚና ላይ ለመቀጠር፣ በDELLT ውስጥ የአመልካች "የሰራተኛ ዓይነት" ከሚከተሉት አንዱ መሆን አለባቸው፦

- መምህር
- ረዳት አስተማሪ
- አሶሺየት(ተባባሪ) ተንከባካቢ
- የተስፋፋ የቤት አቅራቢ
- የቤት አቅራቢ
- ሞንቴሶሪ ረዳት መምህር
- ሞንቴሶሪ መምህር

የሚከተሉት "የሰራተኛ ዓይነቶች" ብቁ አይደሉም፡-

- ዳይሬክተሮች
- በቅድመ-ኬ መጨመሪያ እና መስፋፊያ ፕሮግራም (PKEEP) የመማሪያ ክፍሎች ያሉ መሪ መምህራን
- ከትምህርት ቤት ጊዜ ፕሮግራም ውጪ ያሉ የቡድን መሪዎች እና ረዳቶች
- ረዳቶች እና ተተኪዎች
- በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የህዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) እና በገለልተኛ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ያሉ ሰራተኞች

ብቁነት በስራ ቦታ ምን ተብለው እንደሚጠሩ ከግምት ውስጥ ሳይገባ በDELLT ውስጥ "የሰራተኛ ዓይነት" ላይ የተመሰረተ ነው።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# በ FY23 ውስጥ ተጨማሪ ክፍያዎች እንዴት ይሰራሉ

## *አዲስ የተቀጠሩ/አዲስ ብቁ የሆኑ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች እንዴት ተጨማሪ ክፍያ ያገኛሉ?*

AidKit እያንዳንዱ ሩብ አመት ቀነ ገደብ በፊት አዲስ የተቀጠሩ/ አዲስ ብቁ የሆኑ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች እንዲያመለክቱ ለማመልከቻው ማስፈንጠሪያ ይልካል። ማስፈንጠሪያው በ OSSE ድረ ገጽ ላይም ሊገኝ ይችላል።

የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች በ AidKit መድረክ አማካኝነት ለገንዘብ ድጋፎች ያመለክታሉ።

ብቁነትዎን ለማረጋገጥ፣ AidKit የOSSE የፍቃድ መስጫ ውሂብን ይጠቀማል።

የተፈቀደላቸው አመልካቾች በመረጡት የክፍያ ዘዴ የገንዘብ ድጋፎቻቸውን ያገኛሉ።

ሊረጋገጥላቸው ያልተቻለ አመልካቾች የቀጣይ እርምጃዎች ላይ ትዕዛዞችን ይቀበላሉ።

**የገንዘብ እርዳታዎች መቀበያ ሁለት መንገዶች**

በቀጥታ የባንክ ሂሳብዎ ላይ ማስገባት።

የዴቢ ካርድን በፖስታ ወይም በአካል ለመውሰድ።

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND
AIDKIT
OSSE
WE ARE WASHINGTON DC GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች ከFY24 ጀምሮ በአሰሪዎቻቸው በኩል ተጨማሪ ክፍያ ያገኛሉ

OSSE → AIDKIT →

**FY22**
(ኦክቶበር 1, 2021-ሴፕቴምበር 30, 2022)


OSSE → AIDKIT →

**FY23**
(ኦክቶበር 1, 2022-ሴፕቴምበር 30, 2023)

OSSE → →


**FY24**
(ኦክቶበር 1, 2023-ሴፕቴምበር 30, 2024)

# ነትስ እና ቦልትስ፥ ለተጨማሪ ክፍያ ማመልከት



# በ AidKit አገልግሎት የሚሰጣቸው ፕሮግራሞች


- የተረሱ ሰራተኞች የገንዘብ ድጋፍ የቀጥታ ጥሬ ገንዘብ እርዳታ
- የተረሱ ሰራተኞች የገንዘብ ድጋፍ የኪራይ እርዳታ
- ሚሌ ሃይ ዩናይትድ ዌይ የቀጥታ እርዳታ ለልጅ እንክብካቤ አቅራቢዎች
- የዩታህ የተረሱ ሰራተኞች የገንዘብ እርዳታ የቀጥታ ጥሬ ገንዘብ
- የአደምስ ካውንቲ የዝቅተኛ ገቢ የኮሮናቫይረስ/COVID ፖዘቲቭ መሆን እርዳታ
- የአደምስ ካውንቲ የክትባት ፍትሃዊ ክፍፍል የገንዘብ ድጋፍ
- ሚራክል መኒይ (የተዓምር ገንዘብ)
- ግራንድ ሌክ የንግድ ማገገሚያ የገንዘብ እርዳታ
- የዴንቨር የመሰረታዊ ገቢ ፕሮጀክት




- የተገለሉ የኒው ጀርሲ ኗሪዎች የገንዘብ እርዳታ
- በእጆቿ ውስጥ ዋስትና ያለው ገቢ ፕሮጀክት (In Her Hands Guaranteed Income Project)
  የስደተኞች የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) ኮሎራዶ (Refugee Cash Assistance Colorado)
- የቺካጎ ብርቱ ማህበረሰቦች (Chicago Resilient Communities)
- **የዲሲ የቅድመ ልጅነት አስተማሪዎች ክፍያ ፍትሃዊ ክፍፍል የገንዘብ እርዳታ**

# የራስ ሰር ቁጥጥር የተቀናጀ ስርዓት

ከጫፍ እስከ ጫፍ ለመከታተል ሊለካ የሚችል እና ተያያዥ የተቀናጀ መሠረተ ልማት



# አካታችነትን ከታማኝነት ጋር ማመዛዘን

**አካታችነት**



የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ (ካሽ አሲስታንስ) በተለምዶ የተገለሉ ሰዎች ጋር መድረሱን ማረጋገጥ

**ታማኝነት**



የተቀናጀ የማጭበርበር ጥበቃ እና ተጨባጭ ማረጋገጫ

**የእምነት ፋውንዴሽን**

# በሩብ አመት የማመልከቻ ቀነ ገደቦች

| የሩብ አመት ክፍያ ስርጭት ወር | በሚከተለው ላይ ወይም ከዚያ በፊት መቀጠር አለባቸው | የማመልከቻ ቀነ ገደብ |
|---|---|---|
| ዲሴምበር 2022 | ኖቬምበር 1፣ 2022 | ኖቬምበር 15፣ 2022 |
| ማርች 2023 | ፌብሩዋሪ 1፣ 2023 | ፌብሩዋሪ 15፣ 2023 |
| ጁን 2023 | ሜይ 1፣ 2023 | ሜይ 15፣ 2023 |
| ሴፕቴምበር 2023 | ኦገስት 1፣ 2023 | ሜይ 15፣ 2023 |

- ለFY23 ክፍያዎች የማመልከቻ መቀበያው በኖቬምበር 1፣2022 ተከፍቷል እና እስከ ኦገስት 15፣ 2023 ክፍት ሆኖ ይቆያል። በሜይ 16፣2022 እና ኖቬምበር 1፣2022 መካከል የተቀጠሩ ወይም ወደ ብቁ የሆነ የሰራተኛ አይነት (Staff Type) የተሸጋገሩ ብቁ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች በመጀመሪያው ሩብ አመት ክፍያ ለመቀበል ማመልከቻውን እስከ ኖቬምበር 15፣ 2022 መሙላት አለባቸው።
- ከኖቬምበር 15፣ 2022 በኋላ የተቀጠሩ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች የተጨማሪ ክፍያ ማመልከቻውን ሌላ የአዲስ የሰራተኛ ወረቀቶችን ሲሞሉ እንደ ቀጣይነታቸው አንድ አካል እንዲሞሉት ይበረታታሉ።
- ለማንኛውም የ FY23 ተጨማሪ ክፍያ ተቀባይነት እንዳገኙ፣ ተጨማሪ ማመልከቻዎችን መሙላት አያስፈልጋቸውም፣ ነገር ግን በOSSE ፈቃድ በተሰጠው የልጅ እድገት ፋሲሊቲ ውስጥ በብቁ የሰራተኛ አይነት ውስጥ ተቀጣሪ ሆነው እስከቆዩ ድረስ የቀሩትን FY23 የሩብ አመት አጋማሽ ክፍያዎችን በራስ ሰር ያገኛሉ።


AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# እንዴት ነው ማመልከት የምቻለው

- ማመልከቻ ለማስገባት ሁለት ዘዴዎች አሉ፥
  - የመጋበዣ ማስፈንጠሪያ፥ AidKit ለእያንዳንዱ ሩብ አመት ከማመልከቻው ቀነ ገደብ በፊት በ OSSE የፈቃድ የውሂብ ጎታ ውስጥ አዲስ ለተቀጠሩ እና አዲስ ብቁ ለሆኑ የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪዎች መጋበዣ ማስፈንጠሪያ (በጽሁፍ እና/ወይም በኢሜይል) ይልካል።
    - ማሳሰቢያ፥ ማስፈንጠሪያውን የያዘ የኢሜይል ማሳወቂያ ከ **outreach@ecepayequity.aidkit.org** ይላካል
  - የOSSE ድረገጽ፡- የማመልከቻው ማስፈንጠሪያ በ www.osse.dc.gov/ecepayequity ላይ ይስተናገዳል።
  - ማመልከቻው ኮምፒውተር ወይም የሞባይል መሳሪያን በመጠቀም መሞላት ይችላል።
- ማመልከቻው በእንግሊዝኛ፣ አማርኛ እና ስፓንኛ ይገኛል።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ማመልከቻውን በተለያዩ ቋንቋዎች እንዴት ማግኘት ይቻላል




EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# አስፈላጊ ሰነዶች

- በመንግስት-የተሰጠ ፎቶ ያለው መታወቂያ (የUS ወይም የውጭ-ሀገር)
  - ማሳሰቢያ፥ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈ መታወቂያዎች ይቀበላሉ
- የራስዎ ፎቶ/በራስዎ የተነሳ ፎቶ
- የልጅ እድገት ተቋም የፍቃድ ቁጥር
- ክፍያዎን በቀጥታ ባንክ ማስገባት ለመቀበል የሚመርጡ ከሆነ የባንክ ክፍያ መረጃ (የባንክ ሂሳብ ላይ ያለው ስም/የሂሳብ ቁጥር/የመላኪያ ቁጥር)
- የማህበራዊ ደህንነት ቁጥር (SSN)/የግለሰብ ታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር (ITIN)
- የተሞላ እና የተፈረመ የW-9 ቅጽ (የቅጹ ማስፈንጠሪያ በማመልከቻው ውስጥ ቀርቧል)

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA MURIEL BOWSER, MAYOR

# የማመልከቻ ማሳያ




EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ማመልከቻዬን ካስገባሁ በኋላ ምን ይፈጠራል?

- ማመልከቻዎን ካስገቡ በኋላ፣ የማረጋገጫ ጽሁፍ እና/ወይም ኢሜይል ይደርስዎታል።
- AidKit ማመልከቻዎ ሙሉ መሆኑን እና ብቁነትዎን ለማረጋገጥ ይገመግማል።
  - መረጃዎን ማረጋገጥ ከቻልን፣ ማመልከቻዎ ለክፍያ እንደጸደቀ በ10 ቀናት ውስጥ የምናሳውቅዎት ይሆናል።
  - መረጃቸውን በፍቃድ መስጫ ደታቤዝ ውስጥ መረጋገጥ ያልተቻለ አመልካቾች በማመልከቻ ሂደቱ ውስጥ ቀጥለው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ላይ ተጨማሪ መረጃ ይደርሳቸዋል።
- በአጠቃላይ፣ የሩብ አመት ክፍያዎች ለተፈቀደላቸው አመልካቾች ከ15 ኛው ቀን በኋላ እና በተሰራጨበት ወር የመጨረሻ ቀን ይከፋፈላሉ።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የቴክኒክ ድጋፍ

- በማመልከቻ ሂደቱ ማንኛውም ደረጃ ላይ እርስዎን ለመደገፍ የአመልካች ድጋፍ ልዩ ሙያተኞች ይኖራሉ። ድጋፍ ለመጠየቅ ሁለት አማራጮች አሉ፦
  - ኢሜይል፦ support@ecepayequity.aidkit.org
  - ስልክ፦ በ (202) 831-9298 ይደውሉ እና የድምጽ መልዕክት ያስቀምጡ
    - ድጋፍ ሲጠይቁ እባክዎ ስምዎን፣ የመገናኛ መረጃዎን እና ስለ ድጋፉ ዝርዝር ነገሮችን ያቅርቡ። እባክዎ ያስተውሉ፣ ሁሉም ጥሪዎች በቀጥታ ወደ ድምጽ መልዕክት ይሄዳሉ እና የእርስዎ ጥሪ በደረሰው ተራ ቁጥር ምላሽ ያገኛል።
- የድጋፍ ልዩ ሙያተኞች በብዙ ቋንቋዎች፣ እንግሊዘኛ፣ ስፓንኛ እና አማርኛን ጨምሮ፣ ድጋፍ ለመስጠት የተካኑ ናቸው።

AIDKIT OSSE GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# የመዝጊያ እና ቀጣይ እርምጃዎች



EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ቀጣይ እርምጃዎች

1. ማመልከቻዎን ለመሙላት ዝግጁ እንዲሆኑ የሚከተለውን መረጃ ይሰብስቡ፡-
    a. በመንግስት-የተሰጠ ፎቶ ያለው መታወቂያ
    b. የራስዎ ፎቶ/በራስዎ የተነሳ ፎቶ
    c. የልጅ እድገት ተቋም የፍቃድ ቁጥር
    d. የክፍያ መረጃ (ለምሳሌ፣ ተጨማሪ ክፍያዎን በቀጥታ የባንክ ማስገባት ለመቀበል ከፈለጉ የባንክ መረጃ)
    e. SSN ወይም ITIN

2. የማመልከቻውን ማስፈንጠሪያ ለማግኘት የኤርሊ ቻይልድሁድ አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት የገንዘብ ድጋፍ ድረ ገጽን ይጎብኙ፡- www.osse.dc.gov/ecepayequity

3. ጥያቄዎችን ይላኩ ወይም እርዳታ ይጠይቁ፡
    a. ኢሜይል፥ support@ecepayequity.aidkit.org
    b. ስልክ፥ በ (202) 831-9298 ይደውሉ እና የድምጽ መልዕክት ያስቀምጡ

4. ማመልከቻዎን ይሙሉ እና ያስገቡ!

# የዛሬውን የመረጃ ክፍለ-ጊዜ ስለተካፈሉ እናመሰግናለን!

በቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት ፈንድ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ www.osse.dc.gov/ecepayequityን ይጎብኙ።

የመገልገያ ጽሁፎች፥

- የማመልከቻ ማረጋገጫ ዝርዝር
- የብቁነት እና የክፍያ ፖሊሲ
- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

ስለ ቅድመ ልጅነት አስተማሪ ክፍያ ፍትሃዊነት ፈንድ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ለOSSE.DELCommunications@dc.gov ኢሜይል ያድርጉ።

EARLY CHILDHOOD EDUCATOR PAY EQUITY FUND

AIDKIT

OSSE

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR